**የኢ.ማ.ማ.ተ ዕጩ ተማሪዎች ምዝገባ መስፈርቶች፣ ትዕዛዞችና መመሪያዎች**

**ለመርሃ ግብሩ ለማመልከት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- ዜግነት፡ ኢትዮጵያዊ
- ፆታ፡ ወንድ
- ዕድሜ፡ 25 (የትውልድ ዓመት 1994 እና ከዛ በላይ)
- በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥሩ የመናገርና የመፃፍ ችሎታ ያለው
- ከፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ሪከርድ እንደሌለው የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

- በሜካኒካል፣ ኤሌክትሮ ሜካኒካል፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ አውቶሞቲቭና ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ BSC ዲግሪ ያለው

**የስልጠና መርሃ ግብሩን ለመቀላቀል የሚያስፈልጉ መግቢያ ደረጃዎችና ቅድመ ሁኔታዎች**
**የሚከተሉትን ደረጃዎች በስኬታማነት መጨረስ**

**ደረጃ 1፡ የመለየት ሂደት**

- በኢ.ማ.ት.ኢ. የሚዘጋጅ የጽሁፍ የመግቢያ ፈተና እንዲሁም ለቃለ መጠየቅ ለመጠራት የተቀመጠውን ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል፤
- የመግቢያ ፈተናውን ካለፉ በኋላ ቃለ መጠይቅ በኢ.ማ.ት.ኢ. የቃለመጠይቅ ጉባኤ ለመርሃ ግብሩ ተቀባይነት ማግኘት ያስፈልጋል

**ደረጃ 2፡ የቅበላና ዋስትና ስምምነት መፈረም**

- ዕጩ ተማሪዎችና ዋሶች የቅበላ ስምምነቱን ከመፈረማቸው በፊት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤

**ሰነዶች**

- **ከተማሩበት ዩኒቨርሲቲ የዲሲፕሊን ማረጋገጫ ደብዳቤ -** ተማሪው በካምፓስ ቆይታው ምንም ዓይነት የስነ-ምግባር ችግር እንዳልነበረው የሚያሳይ
- ስልጠና ከጀመረ ቢያንስ ከስድስት ወር በኋላ የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃ የፀና የቀበሌ መታወቂያ
- ፋይዳ መታውቂያ
- ፓስፖርት ካለ
- የልደት ካርድ
- ከሁለቱም የቤተሰብ ዋሶች ጋር ያለውን የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና የሚያሳይ ማስረጃ
- ያገባ/ያላገባ ማስረጃ፣ ያገባ ከሆነ የባለቤቱ ፊርማና በአካል መቅረብ አስፈላጊ ነው

**ፈቃዶች**

- የቅበላ እና የዋስትና ስምምነቶች በሚፈረምበት ወቅት የሚፈፀም “የቅድመ ትንበያ ግምገማ” ለመውሰድ የሚፈቅድ ስምምነት

**ዋሶች**

- ሁለት የቤተሰብ አባሎች
- በእጩ ተማሪው እና በቤተሰብ ዋሶች መካከል ያለው ዝምድና ከሶስት ደረጃ የዘለለ መሆን የለበትም፤ ማለትም (እናት፣ አባት፣ እህት፣ የእህት ባል፣ ወንድም፣ የወንድም ሚስት፣ ሴት አያት፣ ወንድ አያት፣ አክስት፣ አጎት፣ የአክስት ልጅ እና የአጎት ልጅ)

**ዋሱ የዋስትና ሰነዱን ከመፈረሙ በፊት የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል**

- የፀና እና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ (ዋናው እና ኮፒ)
- ዋሱ/ሷ ያገባ/ች ከሆነ የጋብቻ የምስክር ወረቀት (ዋናው እና ኮፒ)፣ ዋሱ/ሷ ያላገባ ከሆነ የቀበሌ መታወቂያውን ከሰጠው አካል እንዳላገባ የሚገልጽ ማስረጃ ማምጣት አለበት/ባት
- ዕጩ ተማሪው እና ዋሶቹ ያገቡ ከሆኑ የእጩ ተማሪው እና ዋሶቹ የትዳር አጋር በአካል ቀርበው የቅበላ/ዋስትና ስምምነቶቹን መፈረም አለባቸው
- ዋሱ/ሷ ከሚሰራበት/ከምትሰራበት መ/ቤት ወርሃዊ ደመወዝ የሚገልጽ (ደመወዝ ከ5,000 ብር ያላነሰ መሆን አለበት)፣ ቋሚ ሠራተኛ መሆኑን/ኗን፣ በተጨማሪም ሠራተኛው/ዋ መ/ቤቱን ቢለቅ/ብትለቅ መ/ቤቱ አስቀድሞ የሚያሳውቅ መሆኑ በደብዳቤው ላይ መጠቀስ አለበት
- የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ - የቤት ካርታ ወይም የመኪና ሊብሬ
- የፖስታ ሳጥን ቁጥር - ዕጩ ተማሪው የሚገኙበት አድራሻ
- ለድርጅታችን የሚፃፉ መረጃዎች በሙሉ **"ለኢትዮጵያ ማሪታይም ትሬኒንግ ኢንስቲትዩት"** ተብለው መፃፍ ይኖርባቸዋል፡፡፡፡

**ደረጃ 3፡ የህክምና ምርመራ፡** የህክምና ምርመራው የሚደረገው በአዲስ አበባ እና በባህርዳር ከተማ ብቻ ሲሆን የዋስትና ስምምነቶችን ከመፈረማቸው በፊት ተቋሙ እውቅና በሰጠው ክሊኒክ ብቻ የሚደረግ ይሆናል

**ደረጃ 4፡** የቅበላ እና የዋስትና ስምምነቶች ከተፈረሙ በኂላ በባህርዳር መሠረታዊ የደህንነት ስልጠና የሚደረግ ነው

**ማሳሰቢያ፡** የቅበላ ስምምነቱ የፀና የሚሆነው ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

**የኢ.ማ.ት.ኢ. አድራሻ**

- **አዲስ አበባ:**
  - አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ቸርችል ጎዳና፣ ትራኮን ህንፃ 8ኛ ፎቅ
  - ስ.ቁ. 0930-00-0621
  - ኢ-ሜይል፡ Bsisay@emacrew.com
- **ባህርዳር፡**
  - ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ፔዳ ካምፓስ፣ ማሪታይም አካዳሚ
  - ስ.ቁ.፥ 0935-98-36-38
  - ኢ-ሜይል፡ TBerhane@emticorp.com